በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 2


**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com


***<u>ቦታ፡-</u>*** **ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**

**በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት** ከ12፡30 – 1፡30

**ሰኔ ፮ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.**

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 2

***ቤተ ክርስቲያን ተነሳሕያኑ ከልብ ለንስሐ መዘጋጀታቸውን የምትመረምርባቸው ቀኖናዊ መንገዶች***

- ጾም (መታቀብ)
- ስግደት
- ምጽዋት
- በበደሉ ጊዜ ቅዱስ ቁርባንን ሳይቀበሉ ለጥቂት ጊዜ መቆየታቸው
- የሰረቁትን፣ የቀሙትን ወይም አታለው የወሰዱትን መመለስ
- የበደልነውን ይቅርታ መጠየቅና ለተበደልነው ይቅር ማለት
- ከእግዚአብሔር ምሕረትን ለማግኘት ስንል ዘወትር ከምንጸልየው ጸሎት ጨምረን መጸለይ
- የቤተ ክርስቲያን ቀኖናት የኃጢአተኞችን ቁስል ለመፈወስ የተሰናዱ ተነሳሕያኑን ከልብ እንዲጸጸቱና በንስሐቸውም ክብር ለማግኘት የሚያበቁ ብሎም ቀድመን የሠራነውን ኃጢአት ደግመን እንዳንሠራው ኃጢአትን የመጥላት ሕይወት የሚያስጡ መንፈሳዊ መፍትሔዎች ናቸው መቀበል፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 2

## *ንስሐችን ተቀባይነት ያለው እንዲሆን የምንከተላቸው መንገዶች*

1. ለእግዚአብሔር ካለን ፍቅር የተነሳ በእውነት ንስሐ መግባት፡- ቅጣትን ወይም ፍርድን ከመፍራታችን የተነሳ ሳይሆን የእግዚአብሔርን የይቅርታ ጸጋና ዘላለማዊ ሕይወትን መውረስን ግብ አድርገን ንስሐ መግባት፡፡
2. ጌታችን ‹‹ነፍሱን የሚወድ ያጠፋታል›› *ዮሐ 12፡25፡፡* እንዳለን ያለመወላወል ለራሳችን ታማኝ ሆነን መገኘት፡፡
3. ኃጢአትንና ምንጩንም ለማድረቅ የተረጋገጠ አቋምና ጽኑዕ ፍላጎት በውስጣችን ማሳደር፡፡
4. በኀልዮ፣ በነቢብ፣ በገቢር የሠራነውን ኃጢአት ለይተን ለማወቅና ዳግመኛም ከተመሳሳይ ኃጢአት ለመራቅ እንችል ዘንድ ራሳችንንና ኅሊናችንን መመርመር፡፡
5. ቅዱስ ጴጥሮስ ለሐናንያ ‹‹ሐናንያ ሆይ፥ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ?›› *የሐዋ 5፡3፡፡* ብሎት እንደነበር የንስሐ አባትን መዋሸት መንፈስ ቅዱስን መዋሸት እንደሆነ ተረድተን ኃጢአታችንን ስንናዘዝ ታማኞች ሆነን መገኘት ፡፡
6. ምስጢርንና የተደበቀ ሐሳብን መግለጥ፡- የንስሐ አባታችን የሚሻለውን መፍትሔ ሰጥቶን በመንፈሳዊ ሕይወታችን መታደስ እንችል ዘንድ ነቢዩ ኤርምያስ ‹‹ተነሺ፥ በሌሊት በመጀመሪያ ክፍል ጩኺ፥ በጌታም ፊት ልብሽን እንደ ውኃ አፍስሺ፡፡›› *ሰቆ ኤር 2፡19* እንዳለን መናዘዝ፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 2

## *ንስሐችን ተቀባይነት ያለው እንዲሆን የምንከተላቸው መንገዶች*

7. ኑዛዜ ስለሠራነው ኃጢአት ራስን መክሰስና መውቀስ እንጂ ሌላውን መክሰስና መውቀስ አይደለምና ምክንያት የምናበዛ አለመሆን፡፡ ይህን አስመልክቶም ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹*ሥጋህን በኃጢአት እንዳያስተው ለአፍህ አርነት አትስጥ፥ በመልአክም ፊት፡፡ ስሕተት ነበረ አትበል እግዚአብሔር በቃልህ ይቈጣ ዘንድ የእጅህንም ሥራ ያጠፋ ዘንድ ስለምን ትሻለህ?*›› ***መክ 5፡6፡፡*** በማለት ይመክረናል፡፡
8. ከመጠን በላይ ገር ወይም ጨካኝ፣ ተጠራጣሪ ወይም ብስጩ ሳንሆን በበሰለ ሁኔታ በግልጽነት ኃጡጠአትን መናዘዝ፡፡
9. ተናዛዡ የንስሐ አባቱ በሚሰጠው ምክርና መመሪያ ሳይናወጽ ተጠቃሚ መሆኑ ለነፍሱ መንፈሳዊ መፍትሔን ለማግኘት ይረዳዋል ብሎ መቀበል፡፡
10. ከንስሐ አባቱ የተሰጠውን ቀኖና በፍቅርና በትዕግሥት ተግባራዊ ማድረግ፡፡ ‹‹*በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፡፡*›› ***ፊል 2፡12፡፡***
11. የንስሐ አባታችን በኑዛዜአችን ላይ ተጨማሪ ነገር ጠይቆን እንደሆነ ካህኑ አባታችን ለራሳችን የሚጠቅመንን የተሻለውን ምክር ሊሰጠን እንደሆነ በመረዳት ሳናማርርና ሳንደብቅ ሁሉን ግልጽ አድርገን ምላሽ መስጠት መቻል፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 2

## *ንስሐችን ተቀባይነት ያለው እንዲሆን የምንከተላቸው መንገዶች*

12. እግዚአብሔር ‹‹ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች፡፡›› *ኢሳ 1፡18፡፡* እንደተናገረው ተናዛዡ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት መዋቀስ አለበት፡፡

13. ንስሐችንንና ቀኖናችንን ፈጽመን ይቅርታን ካገኘን በኋላ የንስሐን በር ከፍቶ አደገኛ ከሆነው ከሞት መንገድ ያዳነንን እግዚአብሔርን እንደ ነቢዩ ኢሳይያስ ‹‹ክፋት እንደ እሳት ይቃጠላል ኵርንችቱንና እሾሁን ይበላል ጭፍቅ የሆነውንም ዱር ያቃጥላል፥ ጢሱም ተትጐልጕሎ እንደ ዓምድ ይወጣል፡፡›› *ኢሳ 9፡18፡፡* ፣ ቅዱስ ጴጥሮስም ‹‹ጌታ እግዚአብሔርን የሚያመልኩትን ከፈተና እንዴት እንዲያድን፥ በደለኞችንም ይልቁንም በርኵስ ምኞት የሥጋን ፍትወት እየተከተሉ የሚመላለሱትን ጌትነትንም የሚንቁትን እየቀጣቸው ለፍርድ ቀን እንዴት እንዲጠብቅ ያውቃል፡፡›› *ካል ጴጥ 2፡9-10፡፡* እንዳለ ብለን ማመስገን አለብን፡፡ ተነሳሕያን በንስሐ ከነዚህ ሁሉ እንደተጠበቁ ሲረዱ በእግዚአብሔር ያላቸው ፍቅር ጥልቅ እየሆነ ኃጢአትን በእግዚአብሔር ኃይል እየተቃወሙ ከርሱ ጋር ለመኖር ፈጽመው የሚሹ ይሆናሉ፡፡ እግዚአብሔርም በሰይጣንና በሠራዊቱም ላይ ድልን ያቀዳጃቸዋል፣ ሰውነታችንንና የሰውነታችንንም በደል ያስተሰርይልናል፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 2

*ንስሐችን ተቀባይነት ያለው እንዲሆን የምንከተላቸው መንገዶች*

14. *መምህራችን ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹›› ኤፌ 6:13* በማለት እንደመከረን ተነሳሕያን ዳግመኛ በፈቃዳችን በኃጢአት እንዳንወድቅ ዘወትር ንጽሕና ባለበት የንስሐ ሕይወት እንድንኖር እንደመከረን መመላለስ፡፡
15. *መንፈሳዊ እድገታችንን ሊያቀጭጭ ስለሚችል ጠንካራ የሆነ አሳማኝ ምክንያት ከሌለን* በቀር ተነሳሒው ሰው ከአንዱ ወደ ሌላው የንስሐ አባት ሲቀያይር አለመገኘት፡፡
16. ተነሳሒው ልክ የሐኪሙን ምክር ተቀብሎ እንደሚጠቀምበት በሽተኛ የንስሐ አባቱን ምክር ተቀብሎ ተጠቃሚ ለመሆን ይችል ዘንድ ጥልቅ የሆነ ፍቅርና መታመን በንስሐ አባቱ ላይ እንዲኖረው መሆን፡፡

- ባለትዳሮች በምስጢረ ተክሊል አንድ ሆነዋልና አንድ የንስሐ አባት እንዲኖራቸው መሆን፡፡ አንድ የንስሐ አባት መኖሩም ከሌላ አቅጣጫ ትዳሩን ለመፈተን የሚመጡ እቅፋቶችን መግቢያ እንዳይኖራቸው በማድረግ ይታደጋልና ባለትዳሮች ከአንዱ የንስሐ አባታቸው የወጣ መንገድ እንዳይኖራቸው ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች ትመክራለችም፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 2

## *ለንስሐ አባቶች የሚጠበቁ መሠረታዊ ነገሮች*

1. በሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት የቅስናን ሥልጣነ ክህነት የተቀበለ መሆን፡፡ *ኀል ዜና 26፡18፡፡*
2. ከሊቀ ጳጳሱ ኑዛዜ እንዲቀበልና ለዚህም አገልግሎት ብቁ መሆኑን የሚገልጽ ፈቃድ ያለው፡፡ *ፊል 2፡20*
3. ስለ ነፍስና ጥልቅ ስለ ሆነው የነፍስ ፈቃድ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ባሉ መጻሕፍትና በሰው ሥነ ልቦና ላይ በቂ እውቀት ያለው መሆን፡፡
4. ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት የቀረበ ግኑኝነት ያለው መሆንና የልጆቹንም ችግር ለመፍታት ዘወትር ወደ እግዚአብሔር የሚያመለክትላቸው መሆን፡፡
5. ጠንካራ ስብእና ያለው መሆን፣ ሁለት መልክ ያለው ሰው አለመሆን፣ ማንም ይሁን ማን እውነቱን ለመናገርና ኃጢአተኛውን ለመገሠጽ አለመፍራት፡፡ ‹‹ይህን በሙሉ ሥልጣን ተናገርና ምከር ገሥጽም፤ ማንም አይናቅህ፡፡ ›› *ቲቶ 2፡15፣* ‹‹ምላሱን ከሚያጣፍጥ ይልቅ ሰውን የሚገሥጽ በኋላ ሞገስ ያገኛልና፡፡›› *ምሳ 28፡13፡፡*
6. ምዕመናኑን ምንም ሳይጎዱ ችግሮችን ሁሉ የሚሠሙበት ጠንካራ መንፈስ ያላቸው መሆን፣ ተነሳሒውንም እንደ ልጅ አድርጎ በትዕግሥት መቀበልና ማስተናገድ፣ ኃጢአታቸውንም የሚናዘዙበት ምቹ ሁኔታ እንዲያገኙ አድርጎ ራሱን ማቅረብ፡፡
7. የደካሞችን ድካም ሊሸከም፣ ኃጢአታቸውን ሲናዘዙም ሳይፈርድባቸው ሊናገሩት የሚፈልጉትን ሁሉ ሊሰማ ለወደፊቱም ኃጢአትን ድል የሚያደርጉበትን መንገድ ሊያሳያቸውና የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ምክር ሊመክራቸው የሚቻለው መሆን፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 2

## *ለንስሐ አባቶች የሚጠበቁ መሠረታዊ ነገሮች*

8. *መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የማይጎዳ መንሳዊም ያልሆነ ምክር ከመምከር የተቆጠበና ልጆቹን በመንፈሳዊ ጎዳና የሚመራበት መንፈሳዊ ብቃት ያለው መሆን።*
9. የሰው ልጅ በተፈጥሮ ሂደቱ የሚከሰትበትን ሥነ ልቦናዊ ለውጥ ያወቀና የተረዳ፣ የቤተ ክርስቲያንንም ትምህርቶች መጻሕፍቱንም የተማረ፣ ለእያንዳንዱ ሕመም ተገቢውን መንፈ ሳዊ ሕክምና የሚሰጥ ብሎም ለንስሐ ሕይወት የማይጎዳና የማያስጨንቅ አበረታች መሆን።
10. ኑዛዜ ለመቀበል የሚያበቃው ዕድሜ ያለው፣ የተከበረ፣ የማያወላውልና ልጆቹም የሚሰሙትና የሚታዘዙት መሆን።
11. በሐሳቡ፣ በልቦናው በአንደበቱም ንጽሕና ያለውና ሳያስደነግጥ ኑዛዜያቸውን የሚቀበል።
12. በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የምዕመናኑ ኑዛዜ ለሌላ ወገን የሚገልጥባቸውና የሚያሳፍራቸውም (ምስጢራቸውን አውጥቶ የሚያወራባቸው) በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንደሚቀጣ የተቀመጠለትን ሕግ በመረዳት ምንም ነገር ቢፈጠር የምዕመናኑን ምስጢር የማይገልጥ መሆን።
13. ለሚናዘዙት የሚገባውን ቀኖና መስጠት ይቻለው ዘንድ ሕገ/ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን የተማረና ያወቀ መሆን።
14. ለልጆቹ ባለው ፍቅር ፍጹም ክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲይዙና ስለ ሃይማኖታቸውና መጠበቅና ስለ ምግባራቸው መቃናት የሚጣጣርላቸው በዚህ ሕይወቱም ቅዱስ ጳውሎስን የሚመስል መሆን። ‹‹ልጆቼ ሆይ፥ ክርስቶስ በእናንተ እስኪሣል ድረስ ዳግመኛ ስለ እናንተ ምጥ ይዞኛል።›› ***ገላ 4፡9።***

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 2

*ለንስሐ አባቶች የሚጠበቁ መሠረታዊ ነገሮች*

15. ንስሐ ለመንፈሳዊ ዕድገት መሠረትና ለተነሳሒውም የመደላደል ምንጭ እንደሆነ የሚያምን መሆን፡፡ ተነሳሒው ንስሐ በመግባቱ አምኖ ሳለ የንስሐ አባት ግን የመቀየር ጥያቄ ቢያቀርብ ለተነሳሒው ጥቅም ሲል ፈቃደኛ መሆን፡፡ የንስሐ አባቱ ሊያሰናብተው ፈቃደኛ ባይሆን ምዕመኑ ወደ ክፍሉ ሊቀ ጳጳስ ቀርቦ ሊሰናበት ይችላል፡፡ የንስሐ አባት በምዕመናኑ የግል፣ የትዳር፣ የሥራ ወዘተ አማካሪ እንጂ የራሱን ፍርድና/ሐሳብ በሌላው ላይ በዘፈቀደ በግድ የሚጭን እንዳልሆነ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

16. የንስሐ አባት ሳይኖራቸው ለኑዛዜ የቀረቡ ቢኖሩ ሊያስደነግጣቸው አይገባም፡፡ ወንድሙ የሆነ ካህን ኑዛዜውን ተቀብሎ ቀናኖ ሰጥቶ ከኃጢአት ማሠሪያ የፈታውንም ሰው አስመልክቶ የወንድሙን የካህኑን አገልግሎት በማክበር የሚቀበል መሆን ይጠበቅበታል እንጂ የሚያቃልልና ምዕመኑንም ግራ የማያጋባ መሆን፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 2

በምስጢረ ንስሐ ካህኑ አባት፣ ፈራጅና መምህር ነው፡፡

*1. አባት*

- የልጆቹ ንስሐ ለመዳኑ ምክንያት እንደሆነ በፍርድ ቀንም ለጌታችን ‹‹እነሆ፥ እኔና እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆች›› *ኢሳ 8፡18፡፡* ብሎ እንደሚመልስ አውቆ ዘወትር መመለሳቸውን ይናፍቃል፡፡ ከቅዱስ ጳውሎስም ጋር ‹‹እናንተ በጌታ ጸንታችሁ ብትቆሙ፥ አሁን በሕይወት እንኖራለንና፡፡›› *ተሰ 3፡8፡፡* ይላል፡፡
- በእያንዳንዱ ቀን የልጁን መመለስ ይጠባበቅ የነበረውንና ሲመለስም ‹‹እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት፥ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው፡፡›› *ሉቃ 15፡20፡፡* እንደተባለው ንስሐውን ተቀብሎ ኃጢአቱን ይቅር ያለውን፣ በመመለሱም ደስታ ያደረገውን ለታላቁም ልጅ ‹‹ዳሩ ግን ይህ ወንድምህ ሞቶ ነበረ ሕያው ስለ ሆነ ጠፍቶም ነበር ስለ ተገኘ ደስ እንዲለን ፍሥሐም እንድናደርግ ይገባናል አለው፡፡›› *ሉቃ 15፡32፡፡* ብሎ የመለሰለትን አባት ይመስለዋል፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 2

**በምስጢረ ንስሐ ካህኑ አባት፣ ፈራጅና መምህር ነው፡፡**

## *2. ፈራጅ*

- ‹‹እውነት እላችኋለሁ፥ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል፡፡›› *ማቴ 18፡18፡፡* ተብሎ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በልጆቹ ጉዳይ ላይ ይፈርዳል፡፡
- ካህኑ ለተቀበለው መለኮታዊ ሥልጣን ቢሠራበት፣ ቸል ቢልበት፣ ሥልጣኑን ተጠቅሞ ቢያስጨንቅ፣ ሥልጣኑን ለግል ጉዳዩ ቢጠቀምበት በሁሉም ተጠያቂ ነው፡፡ ካህኑ ኃጢአት የሠራው ማንም ይሁን ማን በሽተኛውን እንደሚወድና በሽታውን ግን እንደሚጠላ ለማዳንም ማናቸውንም ጠቃሚ መፍትሔዎች እንደሚጠቀም ሐኪም ግልጽ፣ የማያወላውልና፣ የማይፈራ መሆን ይገባዋል፡፡

## *3. መምህር*

- ወደርሱ የሚመጡትን ሁሉ በአግባቡ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት አስተምሮ የጌታችን ደቀ መዝሙር ለመሆን የሚያበቃቸው መምህር ነው፡፡
- የእግዚአብሔርንና በክርስቲያናዊ ሕይወት ስላለው የፍጹምነት መንገድ ተረድቶ ዕውቀቱን፣ ልምዱንና ያለፈበትን ፈተና ሁሉ ተጠቅሞ ያስተምራል፡፡ ፊል 4፡12፣

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 2

**በምስጢረ ንስሐ ካህኑ አባት፣ ፈራጅና መምህር ነው።**

***3. መምህር***

- ለማስተማር ብሎም ልጆቹን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ይሆኑ ዘንድ የሚሻ ካህን ራሱ ለንስሐ አባቱ የታመነና ታዛዥ ደቀ መዝሙር መሆን ይጠበቅበታል። በዚህም መምህራችን ቅዱስ ጳውሎስን በመማር፣ ልምድ በመያዝና በማስተማር ይመስለዋል። ‹‹አሕዛብ እንዲታዘዙ ክርስቶስ በቃልና በሥራ፥ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል፥ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእኔ አድርጎ ከሠራው በቀር ምንም ልናገር አልደፍርም፤ ስለዚህ ከኢየሩሳሌም ጀምሬ እስከ እልዋሪቆን ድረስ እየዞርሁ የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ፤ ሰብኬአለሁ።›› *ሮሜ 15፡18።*
- ልጆቹን ንስሐ ከገቡ ኃጢአታቸውን ከተናዘዙና ቀኖናቸውን (ምስጢረ ንስሐን) ከፈጸሙ በኋላ ሥርየት እንደሚያገኙ ሊያስምራቸው ይገባል። በቅዳሴም ላይ ለሁሉ የሚጸለየው ፍትሐት ዘወልድና ጸሎተ ንስሐ ኃጢአታቸውን አስበው ሥርየትን ለሚሹ ሁሉ እንደሚሆን በማመን በመንበሩ ካለው ከመምህሩ ከጌታችን አምላካችን ዘንድ ለራሱና ለጉባኤው ምሕረትን ይጠይቃል፤ ይደረግለታልም።
- ካህኑ ልጆቹ ከኃጢአት የሚርቁበትን ትምህርትና ጥበብ ዘወትር ሊሰጣቸውና የመልካም ምግባር የሚሆኑበትን ብልሃት ሊያሳያቸው ይገባል። ይህንም ለማድረግ የሚያስተምረውን፣ የተማሩትን፣ የደረሱበትን ደረጃ የሚገመግምበት ማስታወሻ ቢኖረው እጅግ ይመከራል።

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org